# ያ ትውልድ

«ያ ትውልድ ተቋም ልሳን»

ያ ትውልድ ቅጽ 3 ቁጥር 3 የካቲት ፳፱ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ.ም. (March 8, 2016)


## የኢትዮጵያ ሴቶችና ማርች 8

የኢትዮጵያ ሴቶች በተለያየ መልኩ ያበረከቱት አኩሪ አስተዋጽዎ በተለያየ አጋጣሚ ቢገለጽም በርካታ የሴቶች ታሪክ በአግባቡ መዘገብ ገና ይቀረዋል። ሴቶች በተለያየ የሙያ ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽዎ አስመዝግበዋል፣ እያስመዘገቡም ይገኛሉ። ሴቶች ለኢትዮጵያ ሀገራቸው አንድነትና ሉዓላዊነት፣ ለሕዝባቸው መብትና ክብር አኩሪ ተጋድሎ አድርገዋል፣ መስዋዕትነትም ከፍለዋል።

የካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት "የሴቶችን ጥያቄ" ከፍ በማድረግ ሴቶች ከሚደርስባቸው መደባዊ ጭቆናና ምዝበራ በተጨማሪ በፆታቸው የሚደርስባቸውን በደልና አድልዎ ለመስበር ለድርብ ጭቆና ድርብ ትግል ከፍለዋል፣ ማንነታቸውንም አሳይተዋል። ሴቶችን ከማጀትና ከቤት እመቤትነት የዘለለ ሚና እንደሌላቸውና ሚናቸውን በወንዶች ጥገኝነት በመወሰን ዝቅ ብለው እንዲኖሩ ያደረጋቸው የዕምነትና የአጓጉል ባህልና ሥርዓት ጥሎት ያለፈውን አመለካከት ለመቀየር ያላሰለሰ ትግል አድርገዋል።

የኢትዮጵያ ሴቶች በፖለቲካው መስክ ሚናቸው እየጐላ የመጣው የካቲት 66 ግብታዊ አብዮት አስታኮ መሆኑ ባይካድም ለዚህ መሠረታቸው ደግሞ አስከፊው ፊውዳላዊ ሥርዓት ግፍና በደል እንደነበር አይዘነጋም። የካቲት ለእምዬ ኢትዮጵያና ለህዝባቸው የቆሙ ጀግና ትውልድ እንዳበቀለ ሁሉ በርካታ የትግል እመቤቶች አፍርቷል። የትግሉ መሪ ኮከብ በመሆን የታገሉና ያታገሉ ሴቶች የየካቲት 66 ውጤት ነበሩ።

ትውልድና ታሪክ ተያያዥነት አለውና የጀግኖች እናቶቻችን የተጋድሎ ታሪክ በአብዛኛው ሀገርን ከጠላት ወረራ በመከላከል የተመዘገበ ነበር። አርበኛ እናቶቻችን በየጦር ሜዳው ያሳዩት ደጀንነትና ብልህነት ለዛሬ ኢትዮጵያ ህልውና ከፍተኛውን ድርሻ አበርክቷል። "ተከብረሽ የኖርሽው በአባቶቻችን ደም" የምንላት ኢትዮጵያ የእናቶቻችንንም አጥንትና ደም ይዛለች። ለዐድዋ ድል የጣይቱ ብልህነት መሠረት ነው። የውስጥ አርበኛዋ ሸዋረገድ ገድሌ ሚና አስተማሪ ነው። በርካታ ሴት አርበኞች በየዱሩና ጫካው ረግፈዋል። የነኚህ ጀግኖች እናቶቻችን ታሪክና ተጋድሎ ለቀጣይ እህቶቻችን ሀገር ማፍቀርና ለሕዝብ መቆርቆር የመሠረት ድንጋያቸው ነበር። ለሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት ሕይወትን የከፈሉ ሴት እናቶች

ያፈራቻቸው ሀገርና ሕዝብ ተመልካች ፊደል ቀመስ "ዘመናዊ" እህቶች የካቲትን አስታኮ ብቅ ሲሉ ለትግላቸው መሥመር መያዝና ግብ መምታት መደራጀት መፍትሄው እንደሆነ እየተገነዘቡ የመጡበት ወቅት ነበር።

የኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ዓለም አቀፋዊ ትስስርነት ነበረውና ዓለም አቀፍ የላብ አደሮች ቀን እንደሚከበረው ሁሉ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 (የካቲት 29 ቀን) ሴቶች በትግላቸው ማክበር የጀመሩት። ሴቶች በአደባባይ ብቅ ማለት የጀመሩበት ወቅት በሀገራችን ከየካቲት 1966 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጋር ተያያዥነትና ተዛማጅነት አለው። ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 መከበር ደግሞ ሴቶች ተሰባስበውና ተደራጅተው መብታቸውን ያስከብሩ ዘንድ ትግላቸውን ይመሩ ዘንድ በር ከፋች ነበር።

ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በሀገራችን ኢትዮጵያ ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ ሲከበር ሴቶች ለነፃነትና ለሰው ልጆች ሰብአዊ መብት መከበር ካስመዘገቧቸው ተጋድሎና ከከፈሉት መስዋዕትነት ትምህርት በመቅሰም ከሀገራችን ነባራዊ እውነታ ጋር ለማዛመድ እረድቷቸዋል። ሴቶች በፖለቲካው፣ በኤኮኖሚውና በማህበራዊ ህይወት ያላቸውን ሚና ለማጉላት ተደራጅቶ መታገል እንደሚገባቸው ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ትምህርት ሆኗቸዋል።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1911 ጀምሮ በዓለም ሕዝቦች በተለይ በሴቶች መብት ተቆርቋሪዎችና ደጋፊዎች ዘንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲከበር ለኖረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 (የካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም.) 105ኛ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ መልዕክታችን ከ «ያ ትውልድ ተቋም» ይድረሳችሁ።

የካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም የሚከበረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን የዓለም ሴቶች በዓሉን ምክንያት በማድረግ አንድነታቸውን፣ ዓላማቸውንና ተስፋቸውን የሚገልጹበት ዕለት ነው። የኢትዮጵያ ሴቶችም በሀገራችን በረሃብ ለሚሰቃዩ፣ ወደ ባዕድ ሀገር በሽያጭ ለሚጓዙ እህቶቻቸው፣ ያለ ዕድሜያቸው ለወሲብ ጥቃትና አስገድዶ መድፈር ለሚዳረጉ ሕፃናት፣ ጧሪ ላጡ አሮጊት እናቶች፣ አሳዳጊ ላጡ ሕፃናት፣ በተለያየ ሕመም ለሚሰቃዩ እህቶቻችን፣ በየእሥር ቤቱ ለሚማቅቁ እህቶቻቸው፣ በስደት ሕይወት ውስጥ ላሉ... በአጠቃላይ ግፈኛና ዘረኛ አገዛዝ በሴቶች እህቶቻቸው ላይ ያሳረፈውን መከራና ጫና ለመታገል አንድነታቸውን የሚያጠነክሩበት፣ የወደፊት የትግል አቅጣጫቸውን የሚቀይሱበት፣ የሚያቀነባብሩበትና የትግላቸውን መስመር የሚመረምሩበት ቀን ሊሆን ይገባዋል።

ማርች 8 ለሴቶች እህቶቻችን ሀገራቸውን ሕዝባቸውን የሚያዩበት ቀን ናት። ማርች 8 እህቶቻችን ለሰው ልጆች የዜግነት መብትና ነፃነት የሚሞግቱበት ቀን ናት። ማርች 8 እህቶቻችን ከጀግና እናት አባቶቻችን የወረሱትን አኩሪ የሀገር ፍቅር ቅርስ ለትውልድ የሚያስተላልፉበት ቀን ናት። ማርች 8 ለእናት ሀገራችን ኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝቧ እኩልነት ድምጻቸውን ባሰሙ ደማቸው ለፈሰሰው አጥንታቸው ለተከሰከሰው ወገናቸውና በተለይ ሰማዕት ሴቶች እህቶቻችንን የምንዘክርበት ቀን ነው።

እነሆ! እናንት የሕዝብ ድምጾች ጩኸታችሁ አልተነነም፣ ሩጫችሁ አልቆመም፣ ትግላችሁም አልተቀበረም የምንልበት ቀን ማርች 8። ማርች 8 የኢትዮጵያ ሴቶች በዘርና በሃይማኖት ያልተከፋፈለች ኢትዮጵያ ዳግም ትንሳዔዋ ይሆን ዘንድ ወገባቸውን ጠበቅ የሚያደርጉበት የትግል ቀን። ጀግንነትን የሚሠሩ ሺብሬዎችን ለእናት ኢትዮጵያና ለሕዝባቸው ዘብ ይቆሙ ዘንድ ከወርሃ የካቲትና ማርች 8 ተመክሮ ለወጣት እህቶች የሚተላለፍበት ወቅት። ማርች 8 ለብሩህ ተስፋና ለኢትዮጵያ አንድነት የኦሮሞ እናቶች፣ የትግራይ እህቶች፣ የጉራጌ ባልቴቶች፣ የወላይታ ቆኖጃጅት፣ የደቡብ እንስቶች፣ የኦጋዴን አበቦች፣ የአማራ እናቶች ወዘተ ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ዘራችን ኢትዮጵያ፣ ክብራችን ሰንደቅ ዓላማችን ብለው የትግሉ ግማሽ ኃይል፣ እንደቤት እመቤትነታቸው የኢትዮጵያ እመቤትነታቸውን፣ በአንድነታቸው የሚያረጋግጡበት ቀን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ባህሉን መዘከርና ማክበር ስንል ትውልድና ሀገር የሚጠብቁብንን ኃላፊነት መወጣት ማለት ነው። በሀገራችን "የሴቶች ጥያቄ" አልተመለሰምና ማርች 8ን ስንዘክር የጥያቄው ህያውነትን ከግምት በማስገባት ነው። "የሴቶች ጥያቄ" ከሌላው የሀገራችን መሠረታዊ ጥያቄዎች ጋር ተያያዥነት አለውና "የሴቶች ጥያቄ" ከወንዶች በመገንጠል እንደማይፈታ ሁሉ የሀገራችንም ችግር በሀገራችን አንድነት ጥላ ሥር መሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት ሴቶች እህቶቻችን ሚናቸውን የሚጫወቱበት፣ ቃል ኪዳን የሚገቡበት በዓል መሆን ይገባዋል።

እህቶቻችን የእቴጌ ጣይቱን አመራር ብቃትነት ሊወርሱ ይገባል። የነ ድላይ አዋጊነት፣ የነ ዳሮ ነጋሽ አመራርነት፣ የነ መዝገብነሽ ብዕር፣ የነ ሽብሬ መስዋዕትነት፣ የብርቱካን ሚዴቅሳና የርዕዮት ዓለሙ እንግልትና ሌሎች እህቶቻችን የከፈሉት ስቃይና መከራ ለነገ ኢትዮጵያችን ተስፋ ነውና አሁንም ሀገራችን ለአንድነቷና ለክብሯ ሕይወት ፈልጋለችና ማርች 8 ታሪክ የሚሠራበት የመስዋዕትነት ጥሪ ደወል ሊሆን ይገባዋል።

ከየካቲት 66 ዓ.ም ግብታዊ አብዮት ወዲህ የኢትዮጵያ ወጣት ሴቶችና እናቶች አኩሪ የትግል ታሪክ አስመዝግበዋል። የየካቲት ሕዝባዊ ጥያቄ በፋሽስታዊው ደርግ የሥልጣን ጥማት በስድስት ወር ውስጥ አቅጣጫውን ሲስት ከባላባታዊ ሥርዓት ጋር የነበረው የሕዝቡ ትግል፣ ፍልሚያ ከፋሽስታዊ ሥርዓት ጋር ሆነ። ሕዝባዊ ጥያቄዎች አልተመለሱምና ሕዝባዊ ትግሉ ቀጠለ። ለዴሞክራሲ መብት፣ ለሕዝብ መንግሥት ምሥረታ ከደርግ አገዛዝ ጋር በተደረገው ትግል የሴቶች እህቶቻችን ሚና ቀላል አልነበረም።

ታሪክ ነውና በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ከየካቲት አብዮት ዋዜማ ተደራጅቶ በየካቲት አብዮት ማግስት ለሕዝብ ብቅ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ሴቶች እህቶቻችንን በትግሉ በማሳተፍ የኢትዮጵያ ልጆች ያላቸውን የሀገርና ሕዝብ ፍቅር በእህቶቻችንና በእናቶቻችን ዘንድ ምን ያህል እንደተተገበረ ያሳየ የቀዳማይ እመቤቶች ፓርቲ ነበር ቢባል ይገባዋል። ኢሕአፓ ሴቶችን ከማጀት አውጥቶ ለመብታቸው ብቻ ሳይሆን ለሀገርና ለሕዝብ መብት ይሚገቱ ዘንድ "እነሆ ተከተሉኝ!" ሲል መቀነታቸውን አጥብቀው የጎረፉለት እናቶቻችን እህቶቻችን ትብብርና ድጋፍ ሊታመን ከሚገባው በላይ

ነበር። በድል አድራጊነት የሴቶች እኩልነትን ለማሳየት ኢሕአፓ ዕጣው ባይገጥመውም በትግሉ የሴቶችን ማንነትና ጀግንነት ያሳየና ከወንድ እኩል አይደለም በላይ አመራራቸውና ጀግንነታቸው የተመሰከረላቸው በርካታ የትግል እመቤቶች አሳይቷል።

እናቶች ለኢሕአፓ ልጆች የምስጢር ጓዳ በመሆን በርካታ ተግባራት አከናውነዋል። የጠላትን መውጫ መግቢያ በመጠባበቅ ዘብ ቆመዋል። የገበያ ዘምቢላቸውን ለኢሕአፓ ሠነዶች አውለዋል። የምግብ መክተፊያቸውን ለአደፍርስ ማባዣ ጠለላ ሰጥተዋል። የቤት አጥሮቻቸው ወቅታዊ መፈክሮችን አስተናግደዋል። ቤታቸውን ለኢሕአፓ ተግባራዊ ሥራ ሰጥተዋል። በፋሽስቱ ደርግ ቀይ ሽብር ዘመንም በእናትነታቸው ሳይከበሩ ታስረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተገድለዋል። ለልጆቻቸው ስቃይና ሞት አልቅሰው አልወጣላቸውም፣ የቁም መከራን እስከ ዕድሜያቸው ፍጻሜ ያስተናገዱ በርካቶች ናቸው። በከተሞች በየቀበሌውና ከፍተኞች በየክፍላተ ሀገሩ በወረዳና አውራጃ ጭምር ብዕር ያላገኘው፣ ያልተዘገበው አስደናቂና በስተመጨረሻም መሪር ታሪካቸው ቀላል አይደለም።

ወጣት ሴቶች በመሪ አታጋይ ፓርቲያቸው ኢሕአፓ ጥላ ሥርና በኢትዮጵያ ሴቶች ትግላዊ ድርጅት (ኢሴትድ) አማካይነት ከወንዶች እኩል ታግለዋል፣ አታግለዋል የፋሽስት ደርግን አሰቃቂ ስቃይና፣ መከራ ተቀብለዋል። ከፖለቲካው ባሻገር የፋሽስቶች አውሬአዊ ተግባር መወጫ ሆነዋል። ደርግ ማንነቱን በጠመንጃው አስከብሮ ሁሉንም “አንገት አስደፋሁ” ካለ በኋላ እንኳ ሴሰኛ የደርግ አባላትና በየአካባቢው የነበሩ ግልገል ፋሽስቶች ኢሰብአዊ በሆነ መልኩ ሴቶችን በማስገደድ መጫወቻና የርካሽ ስሜታቸው ማርኪያ በማድረግ ለበሽታና ለቁም ሰቆቃና ስቃይ የተዳረጉ እንስቶች ቀላል አልነበሩም። እስከ ደርግ ውድቀት በእርግዝናዋ ለእሥር ተዳርጋና በእሥር ቤት ተገላግላ ሕፃን ልጇን በመከራ ያሳደገችው የብርሃነ መስቀል ባለቤት ታደለች የመከራው ገፈት ቀማሾች ከነበሩ እንስቶች አንዷ ነበረች።

ማርች 8 በኢትዮጵያ ይከበር ዘንድ የሴቶች ትግል ውጤት ነው። ዕለቱ ሴቶች ከመብታቸው በላቀ መልኩ ለሀገራቸውና ሕዝባቸው አንድነትና እኩልነት ያደረጉትንና የሚያደርጉትን ተጋድሎ የሚያስቡበትና የሚያጠናክሩበት ነው። ሴቶች እህቶቻችን ከድኅረ የካቲት 66 ጀምሮ ለትግሉ ያበረከቱትን አስተዋጽዎ የሚቃኙበትና ለትውልድ ምን ሠራን? ምን አድርገን ነበር? መልዕክታቸው የሚተላለፍበት ነው። ሴቶች በፖለቲካው መስክ ብቅ ያደረጓቸውን በቅድመ የካቲት እንደ ማርታ መብራቱን በድኅረ የካቲት በሆዱ ውስጥ ካለው የስምንት ወር ጽንስ ጋር በአረመኔው ደርግ የተገደለችው ነፍሰ ጡሯ ዳሮ ነጋሽን ጨምሮ በየአካባቢው በግፍ የተረሸኑ ወጣት ሴቶች የሚታወሱበት ዕለት ነው። ህያው ታሪካችሁ ከመቃቅብር በላይ ነው! እናስታውሳችኋለን፣ ሀገርና ትውልድ ምንጊዜም ከፍ ከፍ ያደርጓቹዋል እንላቸዋለን።

በኪነ ጥበብና በጽሁፉ ዓለም ሴቶች እህቶቻችን ያበረከቱት አስተዋጽዎ ቀላል አልነበረም። ለአብነት ያህል በጎሕ መጽሔት መዝገብነሽ አብዩንና የመሳሰሉት የሰጡት ድምቀት ቀላል አልነበረም። “እምጻለሁ” ግጥማቸው በርካታ እምቢኝ ለፋሽስት ጀግኖችን አፍርቷል፣ “ልቅሶ አልሻም” ግጥማቸው የጠንካራና ደንዳና እህቶችን ተጋድሎ የፋሽስት መንጋን አስደንብሯል፣

እንደ ኢሕአፓዋ ጀግና ማዘር አሰለፈችን "ከልጆቼ በፊት ሀገሬ" ብላ የአሲምባ እመቤት አድርጓል፣ እንደ ድላይ ጀግና አዋጊዎችን ከሳንጃው ጫፍ አስቀምጧል።

"...ይቺ ጭቁን ምን ታየባት፥ ምን ታየባት
ሴትነቷ እንደ ዕቃ ያስቆጠራት
ይቺ ደሀ ታለቅሳለች . . . ታለቅሳለች
ለኩል ሥራ እኩል ዋጋ ተነፍጋለች
ተደራጂ ታገይ ጓዴ . . . ታገይ ጓዴ
ሀዳሪውን ያን ወንበዴ . . .  ያን ወንበዴ
ተጨቋኟ እህትዬ . . . እህትዬ
ተነሽ ታገይ አያዋጣም ሁሌ እየዬ..."

በሚል ጽንሱን ያደረገው ትግላቸው ለትግሉ ያላቸውን ቆራጥነትና ጠንካራነት ሲገልጹ

"...ልቤ ቆርጦ ተነስቷል
የደም አክታ ያገሳል
በቃ ቆርጫለሁ
አምጫለሁ..."

በማለት ምን ያህል ለትግሉ እስከ መስዋዕትነት ለመጓዝ ያላቸውን ብቃት አሳይተዋል።

«ያ ትውልድ ተቋም» ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን ስናስታውስ የሴቶች እህቶቻችን የትግል ታሪክ ለቀጣይ ሴቶችና አዲስ ትውልድ ትምህርት ይሆን ዘንድ በማስገንዘብ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ ያንዣበበባትን የዘር ፖለቲካ ልትወጣ የሴቶችን ጠንካራ ተሳትፎ ትፈልጋለች። አሁን ባለው አገዛዝ እስከ መታሰርና መገደል የደረሱ በርካታ ሴቶች እህቶቻችን ስቃያቸው ለሀገርና ሕዝብ ነውና ክብር ለናንተ እንላለን። የአሁኑ ትውልድ ወጣት ሴቶች የሀገራችሁን ታሪክ መርምራችሁ ከእናንተ በፊት ከነበሩ ቀደምት ሴት ታጋዮች ጠንካራና ደካማ ጎን ትምህርት ቀስማችሁ ኢትዮጵያን የሁሉም ዘሮች ቤት ታደርጓት ዘንድ ይጠበቃል። "ሸመንደፈራ" እንዳለው ዜመኛ ኢትዮጵያ ቤታችን ለእስላሙም ለክርስቲያኑም አትጠብም። ኢትዮጵያ ገበታዋ በኦሮሞ ጨጨብሳ፣ በጉራጌ ክትፎ፣ በትግራይ አምባሻ፣ በሲዳማ አሚቾ/ብላምቢሎ፣ በሐረር ሰንጋ፣ በአማራ ዶሮ፣ በሱማሌ ወተት፣ ወዘተ ደምቆ፣ የሁሉም ዘሮች ምግብ በጤፍ እንጀራችን በአንድ ማዕድ ቀርቦ፣ ሁሉም ተሰባስቦ ሚሻማባት ትሆን ዘንድ የትግሉ እመቤቶች በማርች 8 ዕይታችሁ ሀገራችሁ ትሁን፣ ጩኸታችሁ ለሁሉም ዘር ሲሆን ኢትዮጵያዊነታችን ከፍ ይላል። ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ዳግም ይታደሳል።

በሴቶች ተሳትፎ የኢትዮጵያችን አንድነት ያብባል!!
ማርች 8 ሰማዕታት እህቶቻችን ሚታወሱበት!
**«ያ ትውልድ ተቋም»**

ኢሜል : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com
ድረ ገጽ : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org
ምስለ ገጽ: yatewlid